## ኦሮሞ ፓለቲካና የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እጣ ፋንታ

## በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ልብ ወለድ

## ክፍል ፯ አውዳመት፣ ካለፈው የቀጠለ

የእኛ በዘመን መለወጫ በዓል ባትደሰትም በበዓል ቀን ቤተሰቡን ማሳዘን አልፈለገችም። በዚያ ላይ የጫልቱ እናት ይመጣሉ ተብሎ ሲጠበቁ አሁንም እዚያ አካባቢ ባለው ሰላም መደፍረስ ምክንያት መምጣት ባለመቻላቸው ባለቤታቸውም፣ ልጃቸው ጫልቱና የልጅ ልጆቻቸው ቅር ብሏቸዋል። ደግነቱ ቅዱስ ዮሐንስ አርብ ቀን ስለዋለ ዋናው በዓል በፆም ቀን በማዋሉ ብዙም ግርግር አልነበረውም።

እነጫልቱ ወደቤታቸው ሲገቡ እግረመንገዳቸውን ለበዓሉ ድምቀት የሚሆን ጉዝጓዝ ይዘው ገብተው ስለነበር የቅዱስ ዮሀንስ እለት ፆመው አረፋፍደው በምሳ ሰዓት አዲሱን አመት አቶ ዳዲ በፀሎት፣ ፈጣሪን አመስግነውና ባርከው ምሳ ተበላ። ጫልቱም ወጉ እንዳይቀር ሞቅ ሞቅ አድርጋ ቡናውም ዳቦውም ቆሎውም ጠላም ሳይቀር ቀርቦ በሰላም አለፈ። ቡና ተጠጥቶ እንዳበቃ የእኛ እረፍት ለማድረግ ወደመኝታ ክፍሏ (ከነጫልቱ ጋር የምትጋራው ክፍል) ገባችና በሀሳብ ተዋጠች ። አመት በዓል በልጅነቷ እንዴት እንደነበር ትዝ አላት። ሰላሙ፣ ፍቅሩ፣ ከጓደኞቿ ጋር ለቅዱስ ዮሀንስ የሚዘምሩት መዝሙር፣ በየቤቱ እየዞሩ የሚጨፍሩት፣ ቤተሰቦቻቸው እንዴት እንደሚወዷቸውና እንደሚመርቋቸው አስታወሰች ።

እነዚያ የታፈኑ የትምህርት ቤት ጓደኞቸ የት ደርሰው ይሆን? በህይወት ይኖሩ ይሆን? ሞት አንዳንድ ጊዜ ከመኖር የሚሻልበት ጊዜ አለ። እኛ ከሞቱት በላይ ካሉት በታች የሆን ፍጡር ነን። እንደሞቱት ነፍስ ይማር አንባልም። የህሊና ፀሎት አይደረግልንም። ቤተሰቦቻችን ልጆቻቸው ሞቱ ተብሎ ተረድተው እርማቸውን አላወጡም። ከታፈነው ተማሪዎች ውስጥ ማን እንደሞተ ማን በህይወት እንዳለ አይታወቅም። እዴፓ ልጆቸ ጠፉብኝ ብሎ እንደማይፈልገን አስመስክሯል። ይባስ ብሎ ለነሽመልስ አብዲሳ የክብር ካባ ይሸልማል። እውነት የታፈኑት ተማሪዎች የትግሬ ወይም የኦሮሞ ቢሆኑ ኑሮ ጦርነት አያውጁም? መንግስት የህዝብን ደህንነት ካላስጠበቀ አለ ይባላል? እያለች ከራሷ ጋር ትሟገት ጀመር።

ምን ሀጢያት ሰርቸ ይሆን ለዚህ መከራ የተዳረግኩት? ብላ በራሷ አዘነች። አሁን እናቴ በዓመት በአል እኔን ስታስታውስ እንዴት ትሆን ይሆን? አባቴስ? ወላጆቿ እሷ እንድትማር የከፈሉት መስዋዕትነት ሁሉ ትዝ አላት። የእኛ ለትምህርት የነበራትን ፍላጎት ስለተረዱ ፈቃዷን ለመሙላት አቅማቸው የፈቀደውን ሁሉ በማድረግ ከፍተኛ ድጋፍ አድርገውላታል። ከወላጆቿ ጋር በጣም ቅርብ ግንኙነት ነበራት። እሷም ከቃላቸው አትወጣም፣ ትምህርትን በተመለከተ ደግሞ የእሷን ሃሳብ ይቀበላሉ።

ብዙ አባቷ የሚያከብሯቸው ሰዎች 12ኛ ክፍል እንደጨረሰች እንዲድሯት ሽምግልና መጥተው እዚህ ከደረሰች ይብቃት ትዳር ብለዋቸው ነበር። አባቷ ግን በጭራሽ መማር እየፈለገች እኔ አልከለክላትም ብለው የከፍተኛ ትምህርት መከታተል እንደምትፈልግና እሳቸውም እንደፈቀዱላት ነግረው ትዳሩን እምቢ ብለው መልሰዋል። ያ ሁሉ በዐይነ ህሊናዋ ሲመጣ አባቴ ትማር ትማር ብየ ልጀን ጉድ ሰራኋት እያለ ይፀፀት ይሆን? ግን እኮ እሱ ጥፋተኛ አይደለም። እሱ እኔ ተምሬ እንደማኮራው ስነግረው እኔን አምኖ፣ የተማሩት የደረሱበትን ስለሚያውቅ እንድማርና ሰው የደረሰበት ቦታ እንደርስለት

ነበር እንጅ፣ በጠገበ የኦሮሞ ጎረምሳ እንደምፈር ቢያውቅ ኑሮ መች ተማሪ ብሎ ይልከኝ ነበር? አለች አባቷን ጥፋተኛ እንዳልሆኑ ለራሷ እያገጋገጠች ።

የእኛን የሚቆረቁራት ነገር የአማራ ወላጆች ዋናው ችግራቸው የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ እነሱ የሚወዱትን ያህል የሚወዳቸው ስለሚመስላቸው ተታለዋል። መንግስት እውነተኛና ትክክለኛ ብቻ ይመስላቸዋልና አዴፓን ያምናሉ። የሚጠላቸው ሊያጠፋቸው የሚፈልግ፣ በጠላትነት የፈረጃቸው፤ አማራን በማጥፋት ኢትጵያዊነትን ለማጥፋት የተደራጀ ቡድን እንዳለ በጭራሽ አይጠረጥሩም። ለዚህ መጠቃታችን ዋናው ተጠያቂ መሆን ያለበት አዴፓን ነው። ለስሙ በአማራ ስም ስልጣን ተቆናጧል። ሁል ጊዜ የሚሰለፈው ደግሞ አማራን ከሚጠላ ወገን ነው። 27 ዓመት ሙሉ በወያኔ ሲያስቀጠቅጠን ኑሮ ዛሬም ለኦዴፓ አድሮ እንዲህ በያለንበት እንድንጠፋ እያደረገ ነው ብላ በቁጭትና በሀሳብ ሰመጠች።

ክፍል ፯ የየእኛ ማስታወሻ ይቀጥላል፡-

*ዘውዲቱ የማነ*

2020-09-18